Australian Government
Department of Social Services

# የቤት ውስጥ እና በቤተሰብ መካከል የሚፈጸም ጥቃት

DSS1816.02.16

እያንዳንዱ ሰው ቤተሰቡ ደስተኛ፣ ጤነኛና ደህንነቱ የተጠበቀ እንዲሆን ይፈልጋል፡፡



ሁላችንም በቤታችንም ሆነ በማህበረሰባችን ውስጥ ከሚፈጸም አመጽ ነጻ የመሆን መብት አለን፡፡



አውስትራሊያ ውስጥ ሴቶችም ወንዶችም እኩል መብት አላቸው፡፡




በቤተሰብ ውስጥ የሚፈጸም አመጽ፣ ጾታዊ ጥቃት፣ በግዳጅ የሚፈጸም ጋብቻ አውስትራሊያ ውስጥ ወንጀል ተደርገው ይቆጠራሉ፤ ምንም እንኳን እነዚህ ቤት ውስጥ ቢፈጸሙም ወንጀል ተደርገው ይቆጠራሉ፡፡ የቤተሰብ አመጽ ማለት መማታት ብቻ አይደለም፡፡ በጣም መጮህ፣ ልጆችን ማስፈራራት፣ የቤተሰቡን ገንዘብ መቆጣጠር እንዲሁም አንደኛውን አጋር ከወዳጆቹ ወይም ከወላጆቹ ጋር እንዳይገናኝ መከልከልን ይጨምራል፡፡



የአውስትራሊያ ፖሊሶች ደህንነትን የሚያስጠብቁ ሲሆኑ ሊታመኑ የሚችሉ ናቸው፡፡




አውስትራሊያ ውስጥ ደህንነት እንዲሰማዎና ደስተኛ እንዲሆኑ የሚያደርጉዎ ለባህል ከፍተኛ ግምት የሚሰጡአገልግሎቶች አሉ፡፡




በሚከተሉት ጉዳዮች ረገድ እርዳታ ማግኘት ይችላሉ፡-

- የቤት ውስጥና የቤተሰብ ጥቃት
- የጾታ ጥቃት
- የግዳጅ ጋብቻ
- የልጅ ጥቃት
- የቃላት ጥቃት




አደጋ ላይ ከሆኑ ፖሊስን በ000 ደውለው ያነጋግሩ፡፡

ምስጢራዊነቱ የተጠበቀ የምክር አገልግሎት እና መረጃ ከፈለጉ
1800 RESPECTን በ1800 737 732 በመደወል ያነጋግሩ፡፡
ወይም www.1800RESPECT.org.au የሚለውን ድረ-ገጽ ይጎብኙ፡፡

የግዳጅ ጋብቻ አደጋ ከተደቀነብዎ የአውስትራሊያን ፌደራል ፖሊስ (Australian Federal Police) በ131 237 ደውለው ያነጋግሩ፡፡

አስተርጓሚ ካስፈለገዎ የትርጉም እና የአስተርጓሚ አገልግሎትን (Translating and Interpreting Service) በ131 450 በነጻ ደውለው ያነጋግሩ፡፡

(C) CALDWorld M: 0419525119